# ፔን ኢንተርናሽናል-በቋንቋ መብቶች ላይ የወጣ የጊሮና ማኒፌስቶ

*ፔን ኢነተርናሽናል የአለም ጸሐፍትን ያቀራርባል፡፡ይህ ማኒፌስቶ በፔን ኢነተርናሽናል የትርጉምና የቋንቋ መብቶች ኮሚቴ ጊሮና ውስጥ ፣ግንቦት ፳፻፫ ዓ.ም የተዘጋጀና በ፸፯ ኛው አለም አቀፍ የልዑካን ጉባኤ፣መስከረም ፳፻፬ዓ.ም የጸደቀ ነው፡፡ማኒፌስቶው ፣ የፔን ኢንተርናሽናልን አስር ዋና ዋና የቋንቋ መብት መሪ መርሆዎችን ይደነግጋል፡፡*

1. ልሳነ ብዙህነት ዋጋ ሊሰሰጠውና ሊጠበቅ የሚገባው የአለም ቅርስ ነው፡፡

2. ለሁሉም ቋንቋዎችና ባህሎች የሚሰጥ ክብር፣ የውይይት ልምድ ለማዳበርና ሰላምን በአለም ላይ ለማስፈን በሚደረገው ሂደት ውስጥ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡

3. ሁሉም ግለሰቦች ህይወት፣ቋንቋ፣ባህልና ማንነት በሚሰጣቸው የማህበረሰብ ልብ ውስጥ መናገርን ይማራሉ፡፡

4. የተለያዩ ቋንቋዎችና የተለያዩ ሓሳብን የመግለጫ ዘዴዎች የመግባቢያ መንገዶች ብቻ ሳይሆኑ በውስጣቸው የሰው ልጆች የደጉባቸውና ባህሎች የተገነቡባቸው ምህዳር ናቸው፡፡

5. ማንኛውም አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ቋንቋውን የአካቢው የስራ ቋንቋ አድርጎ የመጠቀም መብት አለው፡፡

6. በትምህርት ቤት ውስጥ የሚተገበረው የማስተማሪ ዘዴ የአካባቢው ማህበረሰብ የሚናገረው ቋንቋ ክብር ከፍ እንዲል አስተዋጾ ማድረግ አለበት፡፡

7. ዜጎች ስለተለያዩ ቋንቋዎች ጠቅላላ እውቀት እንዲኖራቸው የሚገባ ነገር ነው፡፡ምክነያቱም የሌሎችን ስሜት መገንዘብንና ሙሁራዊ ግልጽነትን እንዲሁም ስለ እራስ ቋንቋ ጥልቅ እውቀት እንዲኖር ያደርጋልና፡፡

8. በሰው ልጆች ዘንድ መከባበርና አንዱ ሌላውን መረዳት እየላቀ እንዲመጣ በሚደረገው ወሳኝ ሂደት ውስጥ ስነጽሑፎችን በተለይም በታላላቅ ባህሎች ላይ የተሰሩትን መተርጎም በጣም ጠቃሚ የሆነውን ክፍል ይይዛል፡፡

9. መገናኛ ብዙሃን፣ ልሳነ ብዙህነትን በአወንታዊ መልኩ ውጤታማ ለማድረግና ክብሩን ለማላቅ፣ ባለ ልዩ መብት ድምጽ ማጉሊያ ነው፡፡

10. የእራስን ቋንቋ የመጠቀምና መጠበቅ መብት በተባበሩት መንግስታት ዘንድ ከመሰረታዊ የሰው ልጆች መብት እንደ አንዱ ሆኖ መቆጠር አለበት፡፡

Translated by PEN